## በተራራማ አካባቢ የሚፈሱ ወንዞችን በዘላቂነት መጠቀምና መጠበቅ

"Sustainable highland River Management in Ethiopia"
በአጭሩ (LARIMA)

### መግቢያ

ይህ ፕሮጀክት በኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት፣ በቦኩ ዩኒቨርሲቲ እና በአምቦ ዩኒቨርሲቲ በጋራ የሚሰራ ሲሆን የገንዘብ ድጋፉን የሚያገኘው APPEAR የሚባል ፕሮገራም ከኦስትሪያ ልማት ማህበር(ADC) ነው። የፕሮጀክቱ ቆይታ ለ ሶስት አመት ሲሆን ይህም ከ ነሀሴ 1፣2015 እስከ ሀምሌ 31 2018 እ.ኤ.አ ነው።

### ለፕሮጀክቱ የተመረጡ ቦታዎች

ፕሮጀክቱ ስራዉን የሚሰራው ከ 1800 ሜትር ከፍታ ባላቸው ቦታዎች ሲሆን በዋናነት በሁለት በተመረጡ ቦታዎች ነው። የመጀመሪያው በአዋሽ ወንዝ መነሻ በጭልሞ ጫካ ውስጥ በሚገኙ ወንዞች ሲሆን ይህም የተመረጠበት ምክንያት አካባቢው በህብረተሰቡና በመንግስት የተጠበቀ በመሆኑ በተሻለ ውሀው ንፁህና ያልደፈረሰ፤ የሰዎች ተፅዕኖ የማይበዛበት በመሆኑ እነደማሳያ/ማወዳደሪያ እንዲያገለግል የተመረጠ ቦታ ነው። ሁለተኛው ቦታ የታችኛው የወንዙ ክፍል ከመጀመሪያው በተለየ ሁኔታ የሰዎች ተፅዕኖ የሚበዛበትና ለልዩ ልዩ ግልጋሎት የሚውል ነው። ይህም ንፁህ ያልሆነውን ወይም የተበከለውን የወንዙን ክፍል እንደማሳያ የሚያገለግለው ነው።



የጭልሞ ጫካ ከፊል



አዋሽ ወንዝ ከመነሻው

### የፕሮጀክቱ ዋና ዋና አላማዎች

- ለህብርታሰቡ ግልፅና ቀላል በሆነ መንገድ የወንዞችንና ምንጮችን ወቅታዊ የጥራት ደረጃ ማወቅና የአጠባባቅ ስልጠና
- የአቅም ግንባታ ለ አምቦ ዩኒቨርሲቲ፣ ለ ኢ.ግ.ም.ኢ. በትምህርት ፣ በምርምርና ስርፀት በዘላቂ የውሀ ሀብት አጠባባቅ እንዲሁም ለተለያዩ አጎራባች ባላድርሻዎች
- በአካባቢው ያለውን አጠቃላይ ከወንዞችና ማንጮች የሚገኘውን ጥቅም የያዘና ስርዓተ ፆታን ታሳቢ ያደረገ መረጃና ዕውቀት
- ሁለት የተመረጡ ቦታዎችን የውሀ ሀብት አጠባባቅን ባማከለ ምርምርና ስልጠና የሚደረግባቸው እንዲሆኑ ማስቻል
- ከፕሮጀክቱ የሚገኘውን ውጤት ለምሁራን፣ ለፖሊሲ አውጪዎች እንዲሁም ለሰፊው ህብረተሰብና ለሚመለከታቸው ሁሉ የማሰራጫ ዘዴዎችን ማዘጋጀት ናቸው።





### ከፕሮጀክቱ የሚገኘው ጥቅም

- የወንዝ የውሀ ጥራትን የጤንነት ሁኔታ በስነ- ህይወታዊ መንገድ በቀላሉ በአካባቢው ህብረተሰብ ማወቅ የሚቻልበት ዘዴ ይወጣል።
- የተለያዩ አዳዲስ እውቀቶችን በስልጠናና በትምህርት እንዲሁም የመማማሪያ መድረኮችና ተግባር ተኮር ስልጠናዎች ይዘጋጃሉ።
- የአካባቢው ህብረተሰብ ቀላል የሆኑ የውሀንና የአካባቢን ንፅህና መጠበቂያ መንገዶችን በተለያዩ ትምህርቶች ያገኛሉ።
- በተመረጡ ሁለት ቦታዎች ላይ ለ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች እንዲሁም ለምርምርና ስልጠና ብሎም ለአካባቢው ህብረተሰብ የማስተማሪያና የ ሰርቶ ማሳያ ቦታዎች ይሆናሉ።
- ከፕሮጀክቱን የሚገኙ አጠቃላይ ውጤቶች በተለያዩ የኮሚኒኬሽን መንገዶች ለተሻለ አሰራር የተዋወቃሉ፤ ይታተማሉ።

